# ትምህርት 17

1. የሴት ዘር የሆኑት ወንዶች የቃየን ዘር የሆኑትን ሴቶች ማግባት ሲጀምሩ ምን ሆነ?

ሀ- እጅግ ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መስማት የማይፈልጉ ሆኑ።

ለ- እጅግ ብዙ ሰዎች የሰይጣንን ትዕዛዝ ብቻ መስማት የሚፈልጉ ሆኑ።

2. እግዚአብሔር «ለሰዎች የምናገረው ለ120 ዓመታት ብቻ ነው» አለ ሰዎች አሁንም እግዚአብሔርን ለመከተል ባለመፈለግ ከጸኑ እግዚአብሔር ምን ያደርጋል?

ሀ- እግዚአብሔር በሞት ይቀጣቸዋል።

3. እግዚአብሔር ለሰዎች ይናገር የነበረው እንዴት ነው?

ሀ- እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለሰዎች ልብ ይናገር ነበር።

4. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለሰዎች ምን ይነግራቸው ነበር?

ሀ- ሰዎች ለእግዚአብሔር እንዲታዘዙ፥ ለሰይጣንን ግን እንዳይታዘዙ ይነግራቸው ነበር።

ለ- ሰዎች የእግዚአብሔርን መንገድ እንዲከተሉ፥ የራሳቸውን መንገድ ግን እንዳይከተሉ ይነግራቸው ነበር።

5. በኖኅ ዘመን የነበሩት ሰዎች ምን ዓይነት ሰዎች ነበሩ?

ሀ- ራስ ወዳዶችና ስግብግቦች።

ለ- ክፉዎችና ዐመፀኞች።

ሐ- የእግዚአብሔርን መንገድ የማይፈልጉ።

መ- የራሳቸውን መንገድ ብቻ የሚፈልጉ።

6. እግዚአብሔር የሰዎችን ኃጢአት አይቷል?

ሀ- አዎን እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን በሙሉ አይቷል።

7. ምድር በሰዎች ኃጢአት ስለ ተሞላች እግዚአብሔር ምን ሊያደርግ ወሰነ?
ሀ- በምድር ላይ የሚኖሩትን ሕይወት ያላቸውን ፍጥረቶች ሁሉ ለማጥፋት ወሰነ።

8. እግዚአብሔር ኖኅን ለማዳን የወሰነው ለምን ነበር?
ሀ- ኖኅ ኃጢአተኛ ሆኖ መወለዱን ያውቅ ስለ ነበረ ነው።
ለ- ኖኅ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መሥራቱን ያውቅ ስለነበረ ነው።
ሐ- ኖኅ እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በሞት እንደሚቀጣ ያውቅ ስለ ነበረ ነው።
መ- ኖኅ ሊያድነው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ያውቅ ስለ ነበረ ነው።
ሠ- ኖኅ እግዚአብሔር ከኃጢአቱ የሚያድነውን አዳኝ እንደሚልክለት ያውቅ ስለ ነበረ ነው።

9. እግዚአብሔር ኖኅ ምን እንዲያደርግ አዘዘው?
ሀ- እግዚአብሔር ኖኅ መርከብ እንዲሠራ አዘዘው።

10. እግዚአብሔር ኖኅ መርከብ እንዲሠራ ያዘዘው ኖኅ በሚፈልገው ዓይነት ነበርን?
ሀ- አይደለም።

11. እግዚአብሔር ኖኅ መርከብ እንዲሠራ የፈለገው እንዴት ነበር?
ሀ- ልክ እግዚአብሔር ባዘዘው ዓይነት ነው።

12. እግዚአብሔር ኖኅ እንዲሠራ ያዘዘው ስንት መርከብ ነበር?
ሀ- አንድ መርከብ ብቻ።

13. እግዚአብሔር ኖኅ ለመርከቡ ስንት በር እንዲያደርግ አዘዘው?
ሀ- አንድ በር ብቻ።

14. ከዚያ በፊት ሰዎች ሁሉ ዝናብ ሲዘንብ አይተው ባያውቁም፤ ኖኅ ያመነው ምንን ነበር?
ሀ- እግዚአብሔር የጥፋት ውኃ እንደሚልክ።

15. ኖኅ መርከቡን እየሠራ ምን ያደርግ ነበር?
ሀ- ኖኅ ሰዎች የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እንዲሰሙና እንዲያምኑ ይነግራቸው ነበር።

- እግዚአብሔር በእርሱ የማያምኑ ሰዎችን በሙሉ ጐርፍ ልኮ እንደሚያጠፋቸው ለኖኅ ነገረው።

- እግዚአብሔር አደርጋለሁ ያለውን ነገር ይረሳል?
- አይረሳም።

- እግዚአብሔር አደርጋለሁ ያለውን ነገር ሁልጊዜ ያደርጋል?
- አዎን።

- አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ።

- አንድ ቀን ልጃችሁ ማሰሮአችሁን ይሰብራል።

- እናንተም ልጃችሁን ትቆጡታላችሁ።

- ልጃችሁን «በኋላ እቀጣሃለሁ» ትሉታላችሁ።

- ሆኖም በኋላ ልጃችሁን መቅጣት ትረሳላችሁ።
- እንዲያውም ልጃችሁ ማሰሮአችሁን መስበሩንም ትረሳላችሁ።

- እግዚአብሔር ግን እንደ ሰዎች አይደለም።

- ሰዎች ይረሳሉ እግዚአብሔር ግን አይረሳም።

- እግዚአብሔር አዳም ከፍሬው ከበላ እንደሚሞት ነገረው።

- አዳም ከዛፉ ፍሬ በበላ ጊዜ ሞተ?
- አዎን።

- እግዚአብሔር ለአዳም የነገረውን ረስቶአል?
- አልረሳም።

- እግዚአብሔር አደርጋለሁ ያለውን አድርጓል?
- አዎን አድርጓል።

- እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከዔድን የአትክልት ስፍራ አባረራቸው።

- እግዚአብሔር እንደ ሰዎች አይደለም።

- እግዚአብሔር አደርጋለሁ ያለውን ነገር ፈጽሞ አይረሳም።
- እግዚአብሔር አደርጋለሁ ያለውን ነገር ሁልጊዜም ያደርጋል።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን አይረሳም።
- እግዚአብሔር ኃጢአትን መቅጣት አይረሳም።

- እግዚአብሔር እያንዳንዱን ኃጢአት ይቀጣል።
- እግዚአብሔር እያንዳንዱን ኃጢአት በሞት ይቀጣል።

- እግዚአብሔር ሰዎች በእርሱ እስኪያምኑ ድረስ ይጠባበቅ ነበር።

- እግዚአብሔር በኖኅ ዘመን ሰዎች በእርሱ እስኪያምኑ ድረስ ለምን ያህል ጊዜ ተጠባበቀ?

- ለ120 ዓመታት።

- እግዚአብሔር ሰዎች በእርሱ እስኪያምኑ ድረስ በሚጠባበቅበት ወቅት፤ በእነርሱ ኃጢአት የተቆጣው ቁጣ ቀንሷል?

- አልቀነሰም።

- እግዚአብሔር ሰዎች በእርሱ እስኪያምኑ ድረስ በሚጠባበቅበት ወቅት በእነርሱ ኃጢአት የተቆጣው ቁጣ እየጨመረ ነው የሄደው።

- እግዚአብሔር በኃጢአት የተቆጣው ቁጣ እየጨመረ ነው የሚሄደው።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን የሚቀጣበት ጊዜ እስኪደርስ ድረስ፥ በኃጢአት ላይ ቁጣው እየጨመረ ነው የሚሄደው።

- ኖኅ መርከቡን ሠርቶ ካጠናቀቀ በኋላ እግዚአብሔር ኖኅን ምን አለው?

ዘፍጥረት 7፡1-4

1- እግዚአብሔር ኖኅን እንዲህ አለው፤ «በዚህ ትውልድ መካከል አንተን ጻድቅ ሆነህ አግኝቼሃለሁና ቤተ ሰብህን በሙሉ ይዘህ ወደ መርከቧ ግባ።
2-ከንጹህ እንስሳት ሁሉ ሰባት ሰባት ተባዕትና እንስት ንጹሕ ካልሆኑት እንስሳት ደግሞ ሁለት ሁለት ተባዕትና እንስት፣
3- እንዲሁም ከወፎች ወገን ሁሉ ሰባት ተባዕትና ሰባት እንስት፣ በምድር ላይ ለዘር እንዲተርፉ ከአንተ ጋር ታስገባለህ።
4- ከሰባት ቀን በኋላ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በምድር ላይ ዝናብ አዘንባለሁ፤ የፈጠርሁትንም ሕያው ፍጡር ሁሉ ከምድር ገጽ አጠፋለሁ።»

- ኖኅ መርከቡን ሠርቶ ካጠናቀቀ በኋላ እግዚአብሔር ኖኅን ምን እንዲያደርግ ነገረው?

- እግዚአብሔር ኖኅ ቤተሰቡን ይዞ ወደ መርከብ እንዲገባ ነገረው።
- እግዚአብሔር ኖኅ እንስሳትንም ደግሞ ወደ መርከብ እንዲያስገባ ነገረው።

- እግዚአብሔር ሰዎችን የሚያጠፋበት ጊዜ ደረሰ።

- እግዚአብሔር ሰዎችን ለማጥፋት የፈለገው ለምንድን ነው?

- ሰዎች ኃጢአተኞች መሆናቸውን ስላላመኑ።
- ሰዎች ኃጢአታቸው ዘላለማዊ ሞት እንደሚገባው ስላላመኑ።

- ሰዎች እግዚአብሔር ብቻ ሊያድናቸው እንደሚችል ስላላመኑ።

- ሰዎች እግዚአብሔር ከኃጢአት የሚያድናቸውን አዳኝ እንደሚልክላቸው የገባላቸውን የተስፋ ቃል ስላላመኑ።

- እግዚአብሔር ሰዎች የራሳቸውን መንገድ ትተው የእርሱን መንገድ እንዲከተሉ ለ120 ዓመታት ያህል ተጠባበቃቸው።

- ነገር ግን ሰዎች የራሳቸውን መንገድ ብቻ መረጡ።

- እግዚአብሔር ለ120 ዓመታት ተጠባበቃቸው።

- እግዚአብሔር ከዚህ በላይ አይጠባበቃቸውም።
- እግዚአብሔር ቅጣቱን የሚሰጥበት ጊዜ ደርሶ ነበር።

- ዛሬም እግዚአብሔር እንደዚሁ ነው።

- እግዚአብሔር ሰዎች የራሳቸውን መንገድ ትተው የእርሱን መንገድ እንዲከተሉ እየጠበቃቸው ነው።

- አንድ ቀን እግዚአብሔር መጠበቁን ያቆማል።

- አንድ ቀን እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ይቀጣል።

ዘፍጥረት 7፡7-11

7- ኖኅና ወንዶች ልጆቹ፣ ሚስቱና የልጆቹ ሚስቶች ከጥፋት ውሃ ለመትረፍ ወደ መርከቧ ገቡ።

8- ንጹሕ ከሆኑትና ንጹሕ ካልሆኑት እንስሳት፣ ከወፎችና በምድር ላይ ከሚሳቡ ፍጡራን ሁሉ ጥንድ ጥንድ፤

9- ተባዕትና እንስት ሆነው ወደ ኖኅ መጡ፤ እግዚአብሔር ኖኅን ባዘዘውም መሠረት ወደ መርከቧ ገቡ።

10- ከሰባት ቀንም በኋላ የጥፋት ውኃ በምድር ላይ መጣ።

11- ኖኅ በተወለደ በ600ኛው ዓመት፣ በሁለተኛው ወር፣ ከወሩም በዐሥራ ሰባተኛው ቀን፣ በዚያ ቀን የታላቁ ጥልቅ ምንጮች በሙሉ ተነደሉ፤ የሰማይ መስኮቶችም ተከፈቱ።

- ኖኅና ቤተሰቡ ወደ መርከቡ የገቡት በየት ነበር?
- በአንዱ በር።

- ሁሉም እንስሳት ወደ መርከቡ የገቡት በየት ነበር?
- በአንዱ በር።

- ይህ በር ብቸኛው የመዳኛ በር ነበር።

- ይህ በር ከእግዚአብሔር ቅጣት የማምለጫ ብቸኛው በር ነበር።

- እግዚአብሔር ኖኅን ያዳነው መልካም ሰው ስለ ነበረ ነውን?
- አይደለም።

- እግዚአብሔር ኖኅን ያዳነው ኃጢአተኛ መሆኑን ስላመነ ነው።

- እግዚአብሔር ኖኅን ያዳነው ኃጢአቱ የዘላለም ሞት እንደሚገባው ስላመነ ነው።

- እግዚአብሔር ኖኅን ያዳነው እግዚአብሔር ብቻ ሊያድነው እንደሚችል ስላመነ ነው።

- እግዚአብሔር ኖኅን ያዳነው እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚልክ ስላመነ ነው።

- ኖኅና ቤተሰቡ እንዲሁም እንስሳቱ ሁሉ ወደ መርከብ ከገቡ በኋላ ምን ሆነ?

ዘፍጥረት 7፡16

16- ከዚያም እግዚአብሔር ኖኅ ላይ ከውጭ ዘጋበት።

- ኖኅ ቤተሰቡና እንስሳቱ ሁሉ ወደ መርከብ ከገቡ በኋላ እግዚአብሔር ምን አደረገ?

- እግዚአብሔር በሩን ዘጋው።
- እግዚአብሔር በሩን የዘጋው ለምንድን ነው?

- በመርከቡ ውስጥ ያሉት እንዲድኑ።
- ከመርከቡ ውጭ ያሉት እንዳይገቡና እንዲሞቱ።

- ከውጭ ያሉት ሰዎች ሲያለቅሱ፥ ኖኅ በሩን መክፈት ይችል ነበር?
- አይችልም።

- ለምን አይችልም?

- እግዚአብሔር በሩን ስለ ዘጋው።

- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ከዔድን የአትክልት ስፍራ ካባረራቸው በኋላ ተመልሰው መግባት ችለው ነበር?

- አልቻሉም።

- ለምን?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር የአትክልቱን ስፍራ ዘግቶ፥ የሚንበለበል ሰይፍ የያዘ መልአክ በበሩ ላይ አቁሞ ስለ ነበር ነው።

- ከእግዚአብሔር ፍርድ ማምለጥ የሚችል አለ?

- የለም።

- እግዚአብሔር በሰዎችን ላይ ሊፈርድ ከወሰነ ማንም ሊያመልጥ አይችልም።

- እግዚአብሔር የመርከቡን በር ከዘጋ በኋላ ዝናብን ሰደደ።

ዘፍጥረት 7፡17-20

17- የጥፋት ውሃም ለአርባ ቀናት ያለማቋረጥ በምድር ላይ ዘነበ፤ ውሃው እየጨመረ በሄደ መጠን መርከቧን ከምድር ወደ ላይ አነሣት።

18- ውሃው በምድር ላይ በጣም እየጨመረና ከፍ እያለ ሲሄድ፣ መርከቧ በውሃው ላይ ተንሳፈፈች።

19- ውሃው በጣም ከፍ በማለቱ፣ ከሰማይ በታች ያሉትን ታላላቅ ተራሮች ሁሉ ሸፈናቸው።

20- ውሃው ከተራሮቹ ጫፍ በላይ 7 ሜትር ያህል ከፍ አለ።

- እግዚአብሔር የጥፋት ውኃ ምድርን በሙሉ እንዲሸፍን ያደረገው እንዴት ነበር?

- በመጀመሪያ እግዚአብሔር ውኃውን ለየው።

- እግዚአብሔር ከፊሉን ውኃ በምድር ላይ አደረገው የቀረውን ደግሞ ከሰማይ በላይ አስቀመጠው።

- ውኃው ምድርን በሙሉ እንዲሸፍን እግዚአብሔር ከሰማይ በላይ ያስቀመጠውን ውኃ በሙሉ አዘነበው።

- ከዚያ በፊት ሰዎች ዝናብ ሲዘንብ አይተው ነበር?
- አላዩም።

- ከዚያ በፊት ሰዎች ዝናብ ሲዘንብ አይተው ባያውቁም እግዚአብሔር ለ40 ቀናት ያህል ዝናብ እንዲዘንብ አደረገ።

- ዓለም በሙሉ በውኃ ተሸፈነ።

- ከፍተኛ ተራሮችና ረጃጅም ዛፎች እንኳን ሳይቀሩ በውኃ ተሸፍነው ነበር።

- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ማድረግ ይችላል።

- ለእግዚአብሔር የሚያቅተው ምንም ነገር የለም።

- ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- ከመርከቡ ውጭ በነበሩት ሁሉ ላይ ምን ደረሰባቸው?

ዘፍጥረት 7፡21-23

21- በምድር ላይ የነበሩ ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ፡- ወፎች፣ የቤት እንስሳት፣ የዱር እንስሳት፣ በምድር የሚርመሰመሱ ፍጡራን፣ ሰዎችም በሙሉ ጠፉ።

22- በአፍንጫቸው የሕይወት እስትንፋስ ያላቸው በየብስ የነበሩ ፍጡራን ሁሉ ሞቱ።

23- ሕይወት ያላቸው ፍጡራን ሁሉ ከምድር ገጽ ጠፉ፤ ሰዎችና እንስሳት፣ በምድር ላይ የሚሳቡ ፍጡራንና የሰማይ ወፎች ከምድር ላይ ጠፉ፤ ኖኅና ከእርሱ ጋር በመርከብ ውስጥ የነበሩት ብቻ ተረፉ።

- ከመርከቡ ውጭ በነበሩት እንስሳት ሁሉ ላይ ምን ደረሰባቸው?
- ሁሉም ሞቱ።

- ከመርከቡ ውጭ በነበሩት ሰዎች ሁሉ ላይ ምን ደረሰባቸው?
- ሁሉም ሞቱ።

- ዛሬ ብዙ ሰዎች ኃጢአተኞች መሆናቸውን አያምኑም።
- ዛሬ ብዙ ሰዎች ኃጢአታቸው የዘላለም ሞት እንደሚገባው አያምኑም።

- ዛሬ ብዙ ሰዎች ከኃጢአታቸው ሊያድናቸው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን አያምኑም።

- ዛሬ ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚልክ፥ የገባውን ቃል አያምኑም።

- ዛሬ ብዙ ሰዎች ከእግዚአብሔር ይልቅ የሰይጣንን ትዕዛዝ ይሰማሉ።
- ዛሬ ብዙ ሰዎች ኃጢአት መሥራትን ይወድዳሉ።

- እናንተስ እንደ እነዚያ ብዙ ሰዎች ናችሁ ወይስ እንደ ኖኅ?

- ከመርከቡ ውጭ ሆኖ መዳን የቻለ አለ?

- የለም።

- እግዚአብሔር ከመርከቡ ውጭ ያሉት ሰዎች በሙሉ እንደሚሞቱ ተናግሯል።

- እግዚአብሔር አደርጋለሁ ያለውን ሁልጊዜ ያደርጋል።

- ከመርከቡ ውጭ ያሉት ሰዎች ሁሉ ከሞቱ በኋላ እግዚአብሔር ምን አደረገ?

ዘፍጥረት 8፡1-4 & 14-19

1- እግዚአብሔር ኖኅንና በመርከቡ ውስጥ ከእርሱ ጋር የነበሩትን የዱርና የቤት እንስሳት ሁሉ አሰበ፤ በምድር ላይ ነፋስ እንዲነፍስ አደረገ፤ ውሃውም ጐደለ።

2- የጥልቁ ምንጮችና የሰማይ ውሃ መስኮቶች ተዘጉ። ዝናቡም መዝነቡን አቆመ።

3- ውሃው ከምድር ላይ ቀስ በቀስ እየቀነሰ መጣ፤ ከመቶ አምሳ ቀን በኋላም ጐደለ።

4- በሰባተኛው ወር፣ በዐሥራ ሰባተኛው ቀን መርከቢ በአራራት ተራሮች ላይ አረፈች።

14- በሁለተኛው ወር፣ በሃያ ሰባተኛው ቀን ምድሪቱ ሙሉ በሙሉ ደረቀች።

15- ከዚያም እግዚአብሔር ኖኅን እንዲህ አለው፤

16- «አንተና ሚስትህ፣ ልጆችህና የልጆችህ ሚስቶች ከመርከቢ ውጡ።

17- እንዲዋለዱ፣ እንዲራቡና በምድር ላይ እንዲበዙ፣ ከአንተ ጋር ያሉትን እንስሳትና በምድር ላይ የሚሳቡ ሕያዋን ፍጡራንን ሁሉ ይዘሃቸው ውጣ። »

18- ኖኅም ከልጆቹ፣ ከሚስቱና ከልጆቹ ሚስቶች ጋር ወጣ።

19- እንስሳቱ ሁሉ፣ ወፎችም፣ በምድር የሚንቀሳቀሱ ሁሉ በየወገናቸው ከመርከቢ ወጡ።

- እግዚአብሔር በመርከቡ ውስጥ ያሉትን ኖኅና ቤተሰቡን አሰበ።

- እግዚአብሔር ዝናቡ እንዳይዘንብ አደረገ፤ በምድር ላይ ያለውን ውሃ እንዲያደርቅ ነፋስን ላከ።

- አንዳንድ ሰዎች ነፋስንና ዝናብን የሚቆጣጠሩት አጋንንት ናቸው ብለው ያምናሉ።

- ያ ውሸት ነው።

- ነፋስንና ዝናብን የሠራው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- የዝናብና የነፋስ ጌታ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- እግዚአብሔር ኖኅና ቤተሰቡን በመርከቡ ውስጥ ሳሉ ጠበቃቸው።

- እግዚአብሔር እንስሳቱን ሁሉ በመርከቡ ውስጥ ሳሉ ጠበቃቸው።

- በመርከቡ ውስጥ ከነበሩት መካከል የሞተ አለ?
- የለም።

- እግዚአብሔር ኖኅና ቤተሰቡን እንደሚያድን ተናገሮ ነበር።

- እግዚአብሔር አደርጋለሁ ያለውን ሁልጊዜ ያደርጋል።

- ኖኅ ከመርከቡ ውስጥ ከወጣ በኋላ ምን አደረገ?

ዘፍጥረት 8፥20-22

20- ከዚያም ኖኅ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ፤ መሠዊያው ላይ ንጹሕ ከሆኑት እንስሳት ሁሉ፣ እንዲሁም ንጹሕ ከሆኑት ወፎች የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ፤

21- እግዚአብሔርም ደስ የሚያሰኘውን መዐዛ አሸተተ፤ በልቡም እንዲህ አለ፤ «ምንም እንኳ ሰው ገና ከልጅነቱ ጀምሮ አሳቡ ወደ ክፋት ያዘነበለ ቢሆንም በእርሱ ምክንያት ሁለተኛ ምድርን አልረግማትም፤ አሁን እንዳደረግሁት ሕያዋን ፍጡራንን ዳግመኛ አላጠፋም።

22- ምድር እስካለች ድረስ፣ የዘር ወቅትና መከር፣ ሙቀትና ቅዝቃዜ በጋና ክረምት ቀንና ሌሊት፣ አይቋረጡም።»

- ኖኅ እግዚአብሔር ስላዳነውና ስለ ተደሰተ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረበ።

- እግዚአብሔር የኖኅን መሥዋዕት ለምን ተቀበለ?

- ኖኅ በእግዚአብሔር ስላመነ ነው።

- ኖኅ የራሱን መንገድ ትቶ የእግዚአብሔርን መንገድ ስለተከተለ ነው።

- የእንስሳት ደም የኖኅን የኃጢአት ዋጋ ከፈለ?

- አልከፈለም።

- ደሙ ኖኅ የኃጢአት ቅጣት ሞት መሆኑን እንዲያውቅ አደረገ።

- ኖኅ መሥዋዕት ካቀረበለት በኋላ እግዚአብሔር ምን አደረገ?

ዘፍጥረት 9፡1-3

1-እግዚአብሔር ኖኅንና ልጆቹን እንዲህ ሲል ባረካቸው፣ «ብዙ ተባዙ፤ ምድርንም ሙሏት፤

2- አስፈሪነታችሁና አስደንጋጭነታችሁ በዱር አራዊት፣ በሰማይ አዕዋፍ፣ በደረት በሚሳቡ ተንቀሳቃሽ ፍጡሮች በባሕር ዓሦች ሁሉ ላይ ይሁን፤ በእጃችሁ ተሰጥተዋል።

3- ሕያውና ተንቀሳቃሽ ፍጡር ሁሉ ምግብ ይሁናችሁ፤ ለምለሙን ዕፅዋት እንደ ሰጠኋችሁ፣ አሁን ደግሞ ሁሉን ሰጠኋችሁ።»

- እግዚአብሔር ኖኅንና ቤተሰቡን ባረከ።

- እግዚአብሔር ኖኅንና ሁሉንም ሰዎች የእንስሳት የወፎችና የዓሦች ሁሉ ጌታ አደረጋቸው።

- እግዚአብሔር ለኖኅ የቃል ኪዳን ምልክትም ሰጠው።

ዘፍጥረት 9፡8 & 11-13

8- እግዚአብሔር ኖኅንና አብረውት ያሉትን ልጆቹን እንዲህ አላቸው፤

11- «ከእንግዲህ ሕይወት ያለው ፍጡር ሁሉ በጥፋት ውሃ እንደማይጠፋ፣ ዳግመኛም ምድርን የሚያጠፋ ውኃ ከቶ እንደማይመጣ ከእናንተ ጋር ኪዳን እገባለሁ።»

12- እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፤ በእኔና በእናንተ መካከል፣ ከእናንተም ጋር ካሉ፤ ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ ጋር ከሚመጣውም ትውልድ ሁሉ ጋር የማደርገው የኪዳኑ ምልክት ይህ ነው።

13- ቀስተ ደመናዬን በደመና ላይ አደርጋለሁ፤ ይህም በእኔና በምድር መካከል ለገባሁት ኪዳን ምልክት ይሆናል።»

- እግዚአብሔር ለኖኅና ለሰዎች ሁሉ የሰጠው ምልክት ምንድን ነው?
- ቀስተ ደመና።

- ቀስተ ደመና የምን ምልክት ነው?

- ቀስተ ደመና እግዚአብሔር ዳግመኛ ምድርን በውኃ እንደማያጠፋ የሚያሳይ ምልክት ነው።

- እግዚአብሔር ዳግመኛ ምድርን በውኃ እንደማያጠፋ የገባውን ቃል ጠብቆአል?

- አዎን።

- ከኖኅ ጊዜ በኋላ እግዚአብሔር ዓለምን በሙሉና በእርሷም ውስጥ ያሉትን በውኃ አላጠፋም።

ዘፍጥረት 9፡18-19

18- ከመርከቧ የወጡትም የኖኅ ልጆች ሴም፣ ካምና ያፌት ነበሩ።
19- ሦስቱ የኖኅ ልጆች እነዚህ ሲሆኑ፣ በምድር ላይ የሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ የተገኙት ከእነዚሁ ነው።

- በምድር ላይ የሚኖሩት ሰዎች ሁሉ ቅድመ አባቶች የሆኑት የኖኅ ልጆች እነማን ናቸው?

- ሴም ካምና ያፌት ናቸው።